# የምንጠይቀው ግድ ስለሚሰጠን ነው

Fred Hutch Cancer Center

Fred Hutch ለሁሉም ታካሚዎቻችን ሁሉን አቀፍ፣ ተደራሽ እና ፍትሃዊ የሆነ ከፍተኛ ጥራት ያለው እንክብካቤ ለመስጠት ቁርጠኛ ነው። ለዚህ ነው እርስዎን እና እንክብካቤ የምናደርግላቸውን ሰዎች ሁሉ ስለ ዘር፣ ቋንቋ፣ የፆታ ማንነት እና ሌሎች የግል መረጃዎች ጥያቄዎችን የምንጠይቀው።

ይህ መረጃ እርስዎን በተሻለ ሁኔታ እንድናውቅ እና የእርስዎን የግል የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች እንድናሟላ ይረዳናል። እንዲሁም ለሁሉም ታካሚዎቻችን የሚኖረውን የእንክብካቤ ተሞክሮ እንድናሻሽል ይረዳናል።

የእርስዎ መረጃ ግላዊ እና በሕግ የተጠበቀ ነው።

ለጥያቄዎች መልስ መስጠት የእርሰዎ ምርጫ ነው። ካልፈለጉ ማጋራት የለብዎትም።

የምንጠይቀው ግድ ስለሚሰጠን ነው።

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**ጥ፡- ምን መረጃ ይጠየቃሉ?**

**መ፡-** የምንጠይቀው የእርሰዎን፡-

- **ዘር፡-** እንደ የቆዳ ቀለም ያሉ አካላዊ ባህሪያትን የሚጋሩ የሰዎች ሰብሰብ። እንዲሁም ተመሳሳይ ማህበራዊ ወይም ባህላዊ ማንነቶችን እና ዳራዎችን ሊጋሩ ይችላሉ። ብዙ የዘር ቡድኖች አሉ እና አንድ ሰው ከአንድ በላይ ቡድን አባል ሊሆኑ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ቡድኖች ሊታወቁ ይችላሉ። ለምሳሌ፡- እስያዊ
- **የዘር ሀረግ ምድብ፡-** ብዙ ጊዜ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው የሚተላለፉ ተመሳሳይ ባህል (እምነት፣ እሴት እና ባህሪያት)፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ የዘር ግንድ ወይም ሌሎች ባህሪያት ያላቸው የሰዎች ሰብሰብ። ለምሳሌ፡- "ሩሲያዊ" ወይም "ኢትዮጵያዊ"
- **ብሄር፡-** ስፔናዊ፣ ላቲኖ/a/x/e እና/ወይም የስፔናዊ ተወላጆች የሆኑ ሰዎች። ሰዎች ከኮስታሪካ፣ ኩባ፣ ፑዌርቶ ሪኮ፣ ደቡብ ወይም መካከለኛው አሜሪካ እና/ወይም ሌላ የሰፔን ጎሳዎች የሚለዩበት የተወሰነ ጎሳ።
- **ቋንቋ፡-** አንድ ሰው ለመግባባት እና ሀሳባቸውን ለመግለጽ የሚፈልጉበት ተመራጭ መንገድ። ለምሳሌ፡- የአንድ ሰው ቀዳሚ ቋንቋ ወይም ሌላ አቀላጥፈው የሚያውቁት ወይም ግንኙነት ለመቀበል ተመራጭ የሚያደርጉት ቋንቋ።
- **የፆታ ዝንባሌ፡-** የአንድ ሰው ለሌሎች ያላቸው ሰሜታዊ እና ወሲባዊ ሰበት።
- **የፆታ ማንነት፡-** የአንድ ሰው ውሰጣዊ የማንነት እና የፆታ ሰሜት፣ ይህም ማለት ወንድ፣ ሴት፣ ሁለቱም ያልሆነ፣ ሁለቱም የሆነ ወይም ሌላም ቢሆን።
- **በወሊድ ጊዜ የተመደበ ፆታ፡-** አንድ ሕፃን ሲወለድ የተመደበው ጾታ (ወንድ ወይም ሴት)፣ ብዙውን ጊዜ በሕፃኑ አካላዊ እና ሌሎች ባዮሎጂያዊ ባህሪያት ላይ የተመሰረተ ነው።
- **የአካል ጉዳተኝነት ሁኔታ፡-** አንድ ሰው አንዳንድ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ እና/ወይም በዙሪያቸው ካለው አለም ጋር መስተጋብር ለመፍጠር የበለጠ አስቸጋሪ የሚያደርግባቸው የአካል ወይም የአዕምሮ እክል ካለባቸው።
- **ማህበራዊ የጤና አነሳሾች ፤** እንደ የተወለዱበት፣ የሚኖሩበት፣ የተማሩበት፣ የሚሠሩበት፣ የሚጫወቱበት፣ የሚያመልኩበት እና ዕድሜያቸው ያሉ በሰው ጤና ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ የሕክምና ያልሆኑ ምክንያቶች።

**ጥ:- ይህን መረጃ ለምን ይጠይቃሉ?**

**መ:-** ለምናገለግላቸው ሰዎች ሁሉ ተገቢውን፣ አካታች እና ከፍተኛ ጥራት ያለው እንክብካቤ መስጠታችንን ለማረጋገጥ ሁሉንም ታካሚዎች እነዚህን ጥያቄዎች እንጠይቃለን። የእርስዎ መልሶች የሚከተሉትን እንድናደርግ ይረዱናል:-

- **ለእርስዎ ተመራጭ እንክብካቤ እንድናቀርብ።** የእንክብካቤ ቡድንዎ ስለእርስዎ የበለጠ ባወቁ ቁጥር፣ የእርስዎን ልዩ ፍላጎቶች በተሻለ ሁኔታ ማሟላት ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ከእንግሊዝኛ ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ ከሆነ፣ አስተርጓሚ ማዘጋጀት ይችላሉ።
- **የጤና አጠባበቅ አለመመጣጠን መቀነስ።** የእርስዎ መረጃ በሁሉም የታካሚ ቡድኖች ውስጥ የተሻሉሁኔታዎችን እና እድሎችን እንድንለይ ይረዳናል። ይህም የአገልግሎታችንን አጠቃላይ ጥራት ለማሻሻል ይረዳናል።
- **የግዛት እና የቁጥጥር መስፈርቶችን ማሟላት።** ታካሚዎችን የስነ ሕዝብ አወቃቀር መረጃን እንድንጠይቅ በሕግ እንገደዳለን። የእርስዎ መረጃ ግላዊ፣ ሚስጥራዊ እና በሕግ የተጠበቀ ነው። ለሕክምና መዝገብዎ መዳረሻ ማግኘት የሚችሉት የእንክብካቤ ቡድንዎ እና ፈቃድ ያላቸው ግለሰቦች ብቻ ናቸው።

**ጥ:- መረጃዬን የሚያየው ማን ነው?**

**መ:-** ሓበሬታኻ ብሕታዊ፣ ምስጢራዊን ብሕጊ ዝተሓለወን እዩ። ናይ ክንክን ጉጅለኻን ፍቓድ ዘለዎም ውልቀሰባትን ጥራይ እዮም ንሕክምናዊ መዝገብካ ክረኽብዎ ዝኽእሉ።

**ጥ:- ከእነዚህ ጥያቄዎች እንዳቸውንም መመለስ የማልፈልግ ከሆነስ?**

**መ:-** የማይፈልጉትን ማንኛውንም ጥያቄ መመለስ የሌብዎትም። ከእነዚህ መረጃዎች ውስጥ የትኛውንም ማቅረብ አማራጭ ነው። የምንጠይቀው ግድ ስለሚሰጠን ነው እና ስለእርስዎ የበለጠ ባወቅን መጠን፣ ለእርስዎ የተሻለ እንክብካቤ መስጠት እንችላለን።

**ጥ:- መረጃዬን ስለማካፈል ሃሳቤን ብቀይርስ?**

**መ:-** መረጃዎን በማንኛውም ጊዜ በMyChart ውስጥ በግል መገለጫዎ ስር ማዘመን ወይም ማስወገድ ይችላሉ። ለMyChart ለመመዝገብ ወይም መዳረሻ ለማግኘት፣ FredHutch.org/MyChart የሚለውን ይጎብኙ። MyChart ከሌለዎት፣ ለእንክብካቤ ቡድንዎ ይንገሩ እና መረጃዎን ያዘምኑልዎታል።

**ጥ:- የእኔ መረጃ እንዴት ነው የሚጠበቀው?**

**መ:-** ሁሉም የግል ማንነት እና የግል የጤና መረጃ በጤና መድህን ተንቀሳቃሽነት እና ተጠያቂነት ሕግ (Health Insurance Portability and Accountability Act, HIPAA) የተጠበቀ ነው።

**ለበለጠ መረጃ**
**ኢሜይል:- healthequity@fredhutch.org**